ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ጥቅምት 15 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**ወያኔና ሼህ መሀመድ አላሙዲ ፍቅራቸው ቀዘቀዘ፤ የሼሁ ንብረት የሆነው ቦታ በአባ ጳውሎስ ተነጠቀ፤ የየመን ባለሀብቶችና የሱዳኑ ቱጃር ወደ ኢትዮጵያ በመግባታቸው ሼሁ አኮረፈ፤ ሰንሻይን የተባለው ድርጅት የወያኔ ባለስልጣናት በሽርክና የሚሰሩበት ነው፤ በደብረዘይት በላይ በግንባታ ሰበብ ከ100 ሺህ ነዋሪዎች ተፈናቀሉ፤ በወያኔ ካድሬዎች መሰሪ ተግባር በዱከም አካባቢ የቻይና ባለሀብቶች እና አርሶ አደሮች ተፋጥጠው ሰነበቱ፤ ሊታጨድ የደረሰ እህል በግሬደር ይታረስ ሲሉ ካድሬዎች ቢወስኑም ህዝቡ በቆንጨራ አባረራቸው፤ በመከላከያ መኮንኖች ላይ የተጀመረው ግምገማ አሁንም እንደቀጠለ ነው፤ የመኮንኖች ቤተሰቦች ከሚኖሩበት መኖሪያ ቤት እንዲወጡ ተወሰነ** >>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ………………**

የወያኔን እድሜ ለማራዘም ሲውተረተር የነበረው ባለሀብት ሼህ መሀመድ አላሙዲ ፒያሳ አካባቢ የነበረውን ቦታ የተነጠቀ መሆኑን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

በወያኔ ተላላኪ የአዲስ አበባ ከንቲባ በነበረው አሊ አብዶ ጊዜ የተሰጠውን መሬት በቅርቡ ንብረትነቱ የቤተክህነት ነው በሚል ለቤተክህነት የተሰጠበት ሼህ መሀመድ አላሙዲ በናዝሬት አካባቢም በሊዝ ገዝቶት የነበረውን ቦታ እንደተቀማ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ዘገባ አስረድቶዋል::

ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር እጅና ጉዋንት ሆኖ ቅልብ ወታደሮች የኢትዮጵያን ህዝብ ሲጨፈጭፉ ድጋፍ ሲያደርግ የነበረው ሼሁ በሰፈሩት ቁና መሰፈር የማይቀር መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለጊዜው ባልታወቀ መንገድ ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር በመቃቃራቸው ከሰባት ዓመት በፊት የተሰጠውን መሬት ሊቀማ እንደቻለ ገልፀዋል::

ከወያኔ ባለስልጣናት በፍቅር እፍ ንፍስ ሲል የኖረው ሺህ መሀመድ አላሙዲ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የቀድሞው ፍቅር ቀዝቅዞ በተለያዩ አካባቢዎች የተሰጠውን መሬቶች የተነጠቀ ከመሆኑም በተጨማሪ ውዝፍ እዳ አለብህ ተብሎ በየአቅጣጫው ጥያቄ እየቀረበበት መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ በጋራ ሲሰራራ የቆየው ሺህ መሀመድ አላሙዲ በዓለም ላይ ካሉ ሀበታሞች ውስጥ ሊ"ተት በበር"ታ የንግድ ዘርፎች ውስጥ ተሰማርቶ ሀብት ሲያግበሰብስ የቆየ ሲሆን፤በቅርቡ ግን በወያኔ ባለስልጣናትና በሼሁ መሀል መራራቅና መቃቃር በመከሰቱ በብዙ መንገድና ምክንያት እየጠለፉት መሆኑን ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

በተለይም በ1997 ዓ.ም ወያኔ ከፍተኛ አደጋ ውስጥ በወደቀበትና ህዝብ በየአደባባዩ በቅልብ ጦር ሲጨፈጨፍ የጀርባ አጥንት በመሆን ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርግ የነበረው ብሎም ለዚህ ያበቃቸው ሺህ አላሙዲን ዛሬ ከተለያዩ ሀገራት በር"ታ ባለሀብቶቹ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት ሲጀምሩ ወትሮም የበላበትን ወጪት ሰባሪ የሆነው የወያኔ ቡድን ሼሁን በተለያዩ መንገዶች መገዝገዝ መጀመሩን ዘገባው ገልፖል፡፡

ከሁለት አመት በፊት ባለ ሃያ አንድ ፎቅ ለመስራት በፒያሳ የተሰጠውን መሬት የቤተክህት ንብረት ነው በሚል የነጠቁት ሲሆን በተመሳሳይ በናዝሬት አካባቢ ብዙ ሺህ ካሬ ሜትር መሬት ተመርቶ በይዞታው ስር የነበረ ቢሆንም በቅርቡ እሱንም የነጠቁት መሆኑን ዘገባው ገልፆ የወያኔ ቡድን ሰውዬውን ከተጠቀመበት በኋላ ሊያሽቀነጥሩት መሆኑን ፍንጭ ሰጪነው ሲል ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

በርካታ የወያኔ ባለስልጣናትን በኢትዮጵያ ህዝብ ንብረት ባለሀብት ያደረጋቸው ሺህ መሀመድ አላሙዲ በአገራችን ውስጥ ያለውን የወርቅ መዕድን ለብዙ አመታት ያለምንም ግብር ሲቸበችብ የነበረና በተለያዩና በበር"ታ የንግድ ዘርፎች ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ ቀንደኛ የወያኔ ደጋፊ እንደነበረ ዘገባው ገልጸዋል፡፡

ወያኔዎች በህዝብ ፊት ተነስተው አረንቋ ውስጥ በተዘፈቁበት ወቅት በገንዘቡ ድጋፍ ከማድረጉም በተጨማሪ በርካታ የውጪ ሀገር ዲፕሎማቶችን በማግባባት ወያኔ ላይ የነበራቸውን መጥፎ አመለካከት እንዲቀይሩ ጥረት ሲያደርግ እንዳልነበረ ዛሬ የየመን ባለሀብቶችና የሱዳን ቱጃር ወደ ሀገር ውስጥ መግባትን ተከትሎ ለሺሁ ፊት የነፈጉት መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አብራርቶል፡፡

በተለይም የየመን ተወላጅ የሆኑና የቢላደን ዘመዶች ናቸው የተባሉ ባለሀብቶች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ሺሁ ደስተኛ ያለመሆናቸውን የገለፀው ዘገባው የሱዳኑ ቱጃር ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር በግልፅና በስውር መገናኘታቸውን ተከትሎ ከፍተኛ ቅሬታ እንዳደረበትም አስረድቷል፡፡

ከግልገል የወያኔ ካድሬ ጀምሮ ቱባ ቱባ ባለስልጣናት ጭምር በሀብት ያንበሸበሸው ሺሁ የጠየቁትን ሳይሆን በልባቸው ያሰቡትን ሁሉ ሳይቀር ይፈፀምላቸው የነበረ ቢሆንም ዛሬ የወያኔ ባለስልጣናት ከአዳዲሶቹ ባለሀብቶች ጋር ፍቅር ስለያዛቸው ሺሁን ገለል ማድረጋቸው የሚያሳዝን ነው ያለው ዘገባው በፒያሳ አካባቢ በተሰጣቸው መሬት ላይ እጅግ ዘመናዊ ህንፃ ለማስገንባት ከ40 በላይ

ገልባጭ ቮልቮ መኪኖችን አስገብቶ ጎድጎድ ማስቆፈር ጀምሮ የነበረ ቢሆንም ወያኔዎች መልሰው የነጠቁት መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልፆል፡፡

በአፄ ኃይለ ስላሴ ግዜ ጀምሮ የመስቀል ደመራ ይበራበት እንደነበርና በደርግ ጊዜም የተለያዩ ክለቦች እግር ኳስ ይጫወቱበት የነበረ መሆኑን የገለፁት አንድ የእድሜ ባለ ፀጋ ከሰባት አመት በፊት ደግሞ ለሺሁ ተሰጠ ተብሎ ታጥሮ የነበረ ቢሆንም አሁን ደግሞ ነጥቀው ለቤተክህነት መስጠታቸው ወያኔዎች ጥቅማቸውን ብቻ የሚያሳድዱ መሆናቸውን የሚያሳይና የሚያስገነዝብ እጅግ አስገራሚና አስደናቂ እርምጃ ነው ሲል ገልፆል፡፡

በሀገር ውስጥ ካሉት የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ውስጥ ዋነኛውና አንጋፋው ሜድሮክ ኢትዮጵያ የተባለው የሺሁ ንብረት የነበረ ቢሆንም ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ግን ሰንሻይን የተባለ የብዙ ባለስልጣናት ሽርክና ያለበት ድርጅት ከመንግስት "ዝና ድጎማ እየተደረገለት ከፍተኛ እንዲደርስ ያደረጉት መሆኑን ዘገባው ገልፆ በዚሁ ድርጅት ካሱ ኢላላ፤ አዜብ መስፍን ፤ አቡነ ጳውሎስ እና ሌሎችም ባለስልጣናት በሽርክና የታቀፉበት በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሦስት መቶ ሚሊዮን ብር በላይ በ1980ዎቹ ውስጥ ብድር ከባንክ የወሰደ ድርጅት መሆኑን የገለፀው ዘገባው በአሁን ሰአት ከአገር ውስጥ ግንባታ በተጨማሪም በአፍሪካ ውስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ በኮንስትራክሽን ስራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ መሆኑንም ዘገባው ገልፆል፡፡

በአገር ውስጥ የተቋቋሙትን የግንባታ ድርጅቶች በተለያዩ ምክንያቶች እያሽመደመዱ የባለስልጣናት ንብረት የሆነው ሰንሻይን ብቻ ጠንክሮ እንዲወጣ ገንዘብ ከባንከ ስራ ደግሞ የመንግሥት ተቋማትን ኮንትራት እየወሰደ እንዲሰራ እየሰጡት ሌሎች ድርጅቶችን ለማዳከም በተለይም የሜድሮክ ኢትዮጵያ የተባለውን የሼሁን ንብረት እንዲሽመደመድ እያደረጉት መሆኑን ዘገባው ገልፆል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ሰንሻይን ተባለው የወያኔ ባለስልጣናት የበሽርክና የተሰገሰጉበት ድርጅት በተለያያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከቻይና ድርጅቶች ባልተናነሰ መልኩ ብዙ የመንገድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ በአዲስ አበባ ገርጂ አካባቢ በተሰጠው ቦታ ላይ ብዙ ሺህ ቤቶችን ገንብቶ በውድ ዋጋ ለሽያጭ ያቀረበ ግዙፍ ኩባንያ ሲሆን አቶ ሳሙኤል በተባሉ ባለሀብት ስም የሚንቀሳቀስ መሆኑንም ውስጥ አዋቂ ምንጮች ያስረዳሉ፡፡

ተወዳዳሪ ነው የተባለው የሺሁ ንብረት ሜድሮክ ኢትዮጵያ በተለያዩ መንገዶች ጫና እያደረጉበት እንቅስቃሴውን እያዳከሙት ብሎም እንዲያቆም  ጥረት እያደረጉ መሆኑን የገለፁት የድርጅቱ ሰራተኞች  ከቅርብ  ጊዜ   ወዲህ የወያኔ ባለስልጣናት ጋር ክፍተት በመፈጠሩ የተነሳ በሁሉም ኩባንያዎቻቸው ላይ  ሰበብ እየፈጠሩ ማዋከብ በመጀመራቸው የቀረ እዳ ክፈል እየተባለ በሸቅርቡ አንድ መቶ ሚሊዮን ብር እንዲከፍል መጠየቁም ሰራተኞቹ ገልፀዋል፡፡

ህዝብ በርሀብና በችጋር እየተጠበሰ ባለበት ወቅት የወያኔ ባለስልጣናት ከአዲስ አበባ ውጪ ደብረ ዘይት ከተማ በሚገኘው ኩሪፍቱ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው መዝናኛ እየተንደላቀቁ እንደሚያሳልፉ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ፡፡

አባ ጳውሎስንም ጨምሮ በርካታ የወያኔ ባለስልጣናት የሚዝናኑበት መናፈሻ ዋጋው እጅግ በጣም ውድ ከመሆኑም በተጨማሪም የባለስልጣናት መዝናኛ በመሆኑም ልዩ ጥበቃ እየተደረገለት እንደሚገኝም ምንጮቹ ገልፀው አገር እና ህዝብን እንመራለን ብለው በህዝብና በአገር ላይ እያሴሩ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት ረሀብ እንደ ሰደድ እሳት ተስፋፍቶ ባለበትና ከ13 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በችጋር እየተጠበሰ  ባለበት በዚህ ወቅት በቀን በቡዙ ሺህ ብር ወጪ እያደረጉ ከመዝናናታቸውም በተጨማሪ ውሽሞቻቸውንና ቅምጦቻቸውን ይዘው የሚሰወሩበት መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ለአገርና ለሕዝብ ምንም ደንታ የሌላቸው የወያኔ ባለስልጣናት የሀገር ሀብትና ገንዘብ ለራሳቸው መቦጥቦጣቸው አልበቃ ብሉቸው ለብጥስጣሽ አገራት መሪዎች ሳይቀር መሬት እያከፋፈሉና በነፃ እያደሉ  ሲሆን በደብረዘይት ሀይቅ አካባቢም ለጅብቲው ፕሬዝዳንት በነፃ ሰፊ መሬት የተሰጣቸው መሆኑን ምንጮች ገልፀዋል፡፡

ለጅቡቲው ፕሬዘደንት ቦታ የተሰጣቸው የወደብ ታሪፍ እናደርጋለን ብለው ማስጠንቀቂያ በሰጡ ማግስት ሲሆን የጅቡቲው ፕሬዝዳንትም ኡመር ጊሌህም በተሰጣቸው እጅ መንሻ  ቦታ ላይ ህንፃ አስገንብተው መዝናኛ ሊከፍቱበት እቅድ እንዳላቸው ምንጮች ጨምረው ገልፀዋል ፡፡

በደብረ ዘይት ሰባት የተለያዩ ሀይቆች የሚገኙ ሲሆን ሆራ ሀይቅና ኩሪፍቱ ሀይቅ ላይ መዝናኛዎች ተገንብተው ስራ የጀመሩ ሲሆን በቅርቡም ብዙ ወያኔ ባለስልጣናት በዘመዶቻቸው ስም ለመገንባት እና ለመስራት ቦታ የወሰዱ ከመሆኑም በላይ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩትን ከአንድ መቶ ሺህ ሕዝብ በላይ የረባ ካሳ ሳይከፍሎቸው እያስነሱዋቸው መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የአገርንና የሕዝብን ሀብት እየዘረፉ በሚስቶቻቸውና በዘመዶቻቸው ስም እያከማቹ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት የዘረፉት ገንዘብ መጠን ከመብዛቱም የተነሳ ቁማር እየተጫወቱበት ነው ያሉት ምንጮች ከደብረዘይት ከተማ ወጣ ብሎ በተሰራው አሮሰ ቁጥር ሁለት ሆቴል ውስጥ ቁማር ሲቀጣቀጡ ውለው የሚያድሩ ሀገራዊና ህዝባዊ ስሜት የሌላቸው ጭፍን የወያኔ "ድሬዎች አሁንም በቅርቡ ስራውን በጀመረው ኩሪፍቱ ሪዞርት ውስጥም በተመሳሳይ ሁኔታ ቁማር ጨዋታ በድብቅ መጀመራቸውን ምንጮች ገልፀዋል፡፡

በተለይም የደብረዘይትን ከተማ ለመቆጣጠር ሲባል በአዲስ አበባ ዙሪያ አርባ አምስት ኪሎ ሚትር ርቀት ድረስ ያሉትን ከተሞች በፌደራል ስር ያስገቡ ሲሆን ይህም ከኦሮምያ ክልል አውጥተው እራሳቸው እነ መለስ እንደፈለጉ ለማሽከርከር እንዲያመቻቸው መሆኑም ታውቋል፡፡

በቅርቡ በደብረዘይት በተወሰደው ሕዝብን የማፈናቀል ዘመቻ በትንሹ ከአንድ መቶ ሺህ ሕዝብ በላይ ያለቤትና መጠለያ የቀሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ለዘመናት ጥረው ግረው የግል ቤት የሰሩት ዜጎችንም እዚህ ግባ የማይባል ሳንቲም እየተሰጣቸው እንደተነሱ ከደብረ ዘይት የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

የባለስልጣናት ንግድ ማዕከል መገንቢያ ይሆናል ተብሎ ሰፊ መሬቶች በሀይቁ ዙሪያ እየታደሉ ከመሆኑም በላይ ዜጎች የትም እየወደቁ፤ በርካታ ሕፃናት በብርድ በሽታ እየተሰቃዩ በአንፃሩ ደግሞ እነሱና እነሱው ብቻ እየተንደላቀቁ እንደሚገኝ የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

በተመሳሳይ በዱከም ከተማ ዙሪያ ጤፍ ተዘርቶ ሊታጨድ በተቃረበበት በዚህ ወቅት ለባለሀብት ተሸጧል በሚል በግዴታ እንዲነሱ ሙከራ መደረጉን ከዱከም የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ለቻይና ባለሀብት የተሸጠው የዱከም ለም መሬት ገበሬዎቹ ሳይሰሙና ሳያውቁ እንዲሁም ካሳ ሳይከፈላቸው ባለፈው ሳምንት ማክሰኞ እለት ሊታጨድ ጥቂት ቀናት የቀረውን አዝመራ ቻይናዎቹ በግሬደር ለማረስ በዝግጅት ላይ እንዳሉ የአካባቢው ነዋሪዎች በዱላና በቆንጨራ ያባረሯቸው መሆኑን ታውቆል፡፡

ሕዝብን የናቁት የወያኔ ካድሬዎች በርሀብና በችጋር ሕዝቡ እያለቀ እያዩት የደረሰ እህልን ለማሳረስ መሞከራቸው ማሰቢያ የሌላቸው ደንቆሮዎች መሆናቸውን ያሳያል ያሉት የአካባቢው

ነዎሪዎች ዱከም ከተማ ዙሪያ በሙሉ ለባለሀብት ተብሎ መሬቱ ተቸብችቦ ያለቀ ሲሆን በር"ታ አርሶ አደሮች እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ እየተፈናቀሉ ለስደት መዳረጋቸውን ዘገባው ጨምሮ ገልፆል፡፡

በሊዝ ስም ለቻይና ባለሀብቶች የተሸጠው ይኸው ሰፊ የእርሻ መሬት ላይ ጤፍ ተዘርቶ ሊታጨድ የደረሰ ሲሆን የአስራ አምስት ቀናት ትዕግስት አዋተው እናርሳለን በማለት ሙከራ በማድረጋቸው የተቆጣው የአካባቢው ህዝብ በቆንጨራና በዱላ ያሳደዳቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ለሊት ህዝቡ በተኛበት ጊዜ ሊያርሱ ይቻላል በሚል ስጋት ሕዝቡ እርስ በርስ ተራ አውጥቶ እየጠበቀ መሆኑን ከዱከም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

በሌላ ዜና በመኮንኖች አዳራሽ ውስጥ የተጀመረው የከፍተኛ መኮንኖች ግምገማ ቀጥሎ እንዳለ ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ከሰባት ቀናት በላይ በወሰደው በዚሁ ግምገማ ላይ የአማራና የኦሮሞ ብሄር ተወላጆችን ለማባረር የዶለተ ከመሆኑም በተጨማሪ የሚባረሩበትን ስልትና ዘዴን ጨምረው እያሴሩ መሆኑን ምንጮች ገልፀዋል፡፡

በዚህም መሰረት እድሜያቸው ለጡረታ ያልደረሱ ቢሆንም የተቃረበ ነው ብለው ያመኑበትን በጡረታ እንዲሁም ወጣት ከሆነ ያገልግሎት ካሳ በሚል በትንሽ ገንዘብ ለማባረር የወጣ እቅድ መኖሩን ምንጮች ገልፀው በተለይም ውጪ አገር ተምረው የመጡት መኮንኖች ጦሩን ሊያሳምፁ ይችላሉ በሚል ስጋት ብቻ የመጀመሪያ የጥቃቱ ኢላማ መሆናቸውን ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ‹የማጥራት ዘመቻ› በሚል በተደረገው የማባረር ዘመቻ ውጭ ሀገር ድረስ ሄደው ለብዙ ዓመታት ተምረው የመጡ መኮንኖች በተለይ የኦሮሞና የአማራ ብሔር ተወላጆች ከመስመራዊ እስከ ከፍተኛ መኮንኖች ድረስ የተባረሩ ሲሆን አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ መኮንኖችን ለማባረር ስም ዝርዝራቸው እየተለቀመ መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

በሳሞራ የኑስ የሚመራው ይኸው የከፍተኛ መኮንኖች ግምገማ ለብዙ ዓመት ወደ ሁዋላ ተመልሶ በ1997 ዓ. ም. በነበረው ግርግር የሩቅ ዘመድ እንኳዋን ሆኖ ተሳትፎ ነበር ከተባለ እና በህወሀት ክፍፍል ወቅት ለነስዬ ድጋፍ ሲያደርግ ነበር ተብለው የተገመቱ በሙሉ የመባረር እጣ

የሚገጥማቸው መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ በተለይም በከፍተኛ መኮንኖች ላይ የምንጠራ ዘመቻው ጠንክሮ የሚቀጥል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በአዲስ አበባ ባለፈው ሳምንት ውስጥ የተጀመረው የመኮንኖች ግምገማ እስከ ታችኛው የጦሩ ክፍል ድረስ እንደሚዳረስ የገለፁት ምንጮቹ በቅርቡ ግምገማ ላይ የጦሩን ሀሳብ ሊያስቀይሩ ይችላሉ ተብሎ የተገመቱ መኮንኖች ከየጦሩ ክፍል ውስጥ እየተመረጡ ግማሾቹ የግዳጅ እረፍት እንዲወጡ ሲደረግ ገሚሶቹ ደግሞ ለእስር እየተዳረጉ እንደሚገኙም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ከ8 ቀናት በላይ በወሰደው በመኮንኖች መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ጄ/ል ሳሞራ የኑስ እየመራ ሲሆን ሌ/ጄ/ል ታደሰ ወረደ ፤ሜ/ጄ/ል ዮሀንስ ገ/መስቀል ፤ሜ/ጄ/ል ሀሰን ኢብራሂም ፤ሜ/ጄ/ል ገዛኢ አበራ፤ ሌ/ጄ/ል ባጫ ደበሌ እና ሌሎችም የተገኙ ሲሆን በዚሁ በተደረገ ግምገማ ላይ አንድም ጄኔራል እንደማይባረር የተነገራቸው ቢሆንም ብዙዎቹ ግን ተግሳፅና ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው ምንጮቹ አጋልጠዋለው፡፡

በጦሩ ውስጥ ምንጠራ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ባሉበት በዚህ ወቅት በአዲስ አበባ ቀድሞ ሲግናል ተብሎ በሚጠራው አ"ባቢ በተገነባው ህንፃ ውስጥ ሲኖሩ የነበሩ የመኮንኖች ቤተሰቦች በአስቸኩዋይ እንዲወጡ ትዕዛዝ የተሰጣቸው መሆኑን ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገለፁ፡፡፡

ባለፈው ሳምንት ጀምሮ የወጣው ይኸው መመሪያ እንደሚያመለክተው ከሆነ ቤተሰቦቻቸው ብቻ በህንፃው ውስጥ የሚኖሩ እንደነበርና አባወራዎቹ መኮንኖች ገሚሶቹ አሰልጣኞች በመሆናቸው በየጦር ትምህርት ቤት ተመድበው እየሰሩ ሲሆን ከፊሎቹ ደግሞ በየጦሩ ክፍል ውስጥ በተለያየ ሙያ ተመድበው እየሰሩ ቢሆንም በሌሉበት ቤተሰቦቻቸው እንዲወጡ ትዕዛዝ መሰጠቱን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ለብዙ ዓመታት መከላከያ ባሰራው ህንፃ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት እነዚህ የመኮንኖች ቤተሰቦች በተሰጣቸው ትዕዛዝ ተደናግጠው መያዣና መጨበጫ ጠፍቶዋቸው ከላይ እታች እያሉ ቢንከራተቱም በጄ/ል ሳሞራ የኑስ ትዕዛዝ የወጣው መመሪያ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ተነግሮዋቸው እንደተመለሱ የገለፁት ምንጮቹ መኮንኖቹ ከያሉበት የጦር ክፍል የሚባረሩት ስም ዝርዝር ውስጥ ሳይኖሩበት እንደማይቀር ምንጮቹ ግምታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

የወያኔ ቡድን የገዛ ጥላውን ስለማያምን በየጊዜው የምንጠራ ዘመቻ እያ"ሄደ ሲሆን አሁንም ከጦሩ ጋር የሚስማማ አዛዥ ጥያቄ ምልክት ውስጥ እየገባ ወደ ተለያዩ ክፍሎች የሚዘዋወር ከመሆኑ በተጨማሪ እንደሚባረር የከዚህ ቀደሙ እርምጃ አመላ"ች ነው ያሉት ምንጮቹ አሁንም በር"ታ መኮንኖችን ለማባረር ዝግጅት መጠናቀቁን እና በአንዳንድ ክፍሎች ተግባራዊ መሆን መጀመሩን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

በዚህም መሰረት በአዋሽ አርባ ወታደራዊ ማሰልጠኛ "ምፕ ውስጥ ሰፍሮ ያለው ጦር አዛዥ በቅርቡ በተደረገው ምንጠራ ከስራው የተሰናበተ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ሌተና ኮሎኔል ደምሴ የተባለው ይኸው የወያኔ ጦር አለቃ የአማራ ብሔር ተወላጅ ሲሆን ከጦሩ ጋር ይቀርብና ይግባባ ስለነበር የጦሩን አቂዋም ሊያስቀር ይችላል በሚል በጡረታ እንዲወጣ መደረጉን ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

ወያኔ በጎንደር ከታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ፤በሰሜን ከሻዕቢያ ፤በምስራቅ እራሱን የኦጋዴን ነፃ አውጭ ብሎ ከሚጠራው  እና ከአልሻባብ ጋር ፍጥጫና ግጭት ውስጥ ገብቶ በሚገኝበት በዚህ ወቅት ልምድና እውቀት ያላቸውን መኮንኖች ጦሩን ሊያሳምፁ ይችላል በሚል ስጋት ብቻ የማባረር ዘመቻውን አስፋፍቶ መቀጠሉ አስገራሚ ነው ሲሉም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

የመከላከያ ሚኒስትርነቱን ቦታ ከአዲስ አበባ ከንቲባነቱ ጋር ደርቦ እየሰራ ያለው የወያኔ ተላላኪ ኩማ ደመቅሳ ለፊርማ "ልሆነ በስተቀር ሁሉንም ስልጣን ተቆጣጥሮ የሚገኘው ጄ/ል ሳሞራ የኑስ መሆኑንም  ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡